## ትምህርት 8

### የሚያመልኩት አምላክ ማንነት ማወቅ

የሚያመልኩት አምላክ ማንነት በተቻለ መጠን ማወቅ በእምነት ለመጽናት ወሳኝ ነገር ነው፡፡

ማቴዎስ 8፡6-10 *"ጌታ ሆይ፤ አገልጋዬ ሽባ ሆኖ እጅግ በመሠቃየት ከቤት ተኝቶአል" አለው። [7] ኢየሱስም፣ "እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ" አለው። [8] የመቶ አለቃው ግን መልሶ እንዲህ አለ፤ "ጌታ ሆይ፤ ወደ ቤቴ እንድትገባ የሚገባኝ አይደለሁም፤ ነገር ግን ከዚሁ ሆነህ አንዲት ቃል ብቻ ተናገር፤ አገልጋዬም ይፈወሳል፤[9] እኔ ራሴ የምታዘዛቸው አለቆች፣ ለእኔም የሚታዘዙ የበታቾች አሉኝ፤ ከእነርሱ አንዱን፣ 'ሂድ!' ስለው ይሄዳል፤ ሌላውን፣ 'ና!' ስለው ይመጣል፤ አገልጋዬንም፣ 'ይህን አድርግ' ስለው ያደርጋል።" [10] ኢየሱስም በመልሱ ተደንቆ ይከተሉት ለነበሩት እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፣ ከእስራኤል መካከል እንኳ እንዲህ ያለ እምነት ያለው አንድ ሰው አላገኘሁም፤"* (አለ)::

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍል አንድ ነገር ግልጽ አድርጎ ያሳየናል፤ ይኸውም በቁሳዊው ዓለም ፍጥረት ሁሉ ከላይ እስከታች በእዝ ሰንሰለት የተያያዘ የመሆኑን ያህል በመንፈሳዊው ዓለምም በሁለት ተቃራኒ ኃይላት ማለትም በእግዚአብሔር ወይም በጨለማው ኃይላት (በሰይጣንና አጋንንቱ) የአገዛዝ የእዝ ሰንሰለት የሚመራ መሆኑን ነው፡ ፡ መንፋሳዊው ኃይል በቁሳዊው ዓለም ላይ የበላይነት ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሰው በመልካሙ እግዚአብሔር ወይም በክፉው ሰይጣን አገዛዝ የእዝ ሰንሰለት ስር ከመሆን ውጪ ሌላ አማራጭ የሌለውና መሃል ሰፋሪ ወይም ገለልተኛ ሆኖ መኖር እንደ ማይቻል ማወቅ ይገባል፡፡

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ሁሉ በፈቃደኝነትና በውዴታ እንዲታዘዘው (እንዲገዛለት) እየጠየቀ ከእርሱ ጋር ተስማምተው መኖር የፈለጉትን ተቀብሎ ያስተዳድራል እንጂ ማንንም ያለፈቃዱ እንዲያምንበትና እንዲገዛለት አያስገድድም፡፡ ሰይጣንና አጋንንቱ ግን ማንኛውም ለእግዚአብሔር ከመገዛት ያፈነገጠን ሰው የእግዚአብሔር ጥበቃ ከሌለው ወደደም ጠላ ምንም ፈቃደኝነት ሳይጠይቁ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንደሌለው ሲያዩ ሰውየው ንስሃ ገብቶ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረቱን ካላስተካከለ ወዲያውኑ ተቆጣጥረው በመግዛት ይቀጥላሉ፡፡

በምድራችን ላይ ከእግዚአብሔር ውጪ በሰዎች አማልክት ተብለው የሚጠሩ ብዙ አማልክት አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው በተለይ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ረገድ አስተማማኝና የሚያስመካ ማረፊያ ሊሆነው የሚችለው አምላክ የቱ መሆኑን በማጤን ሳይለይ፣ እንዲያው ሰው ያመልከዋል ብሎ ማንኛውም አምላክ መከተል፣ መጨረሻው ለዘላለም ኪሳራ የሚዳርገው ስለሆነ ሊከተለውና ሊገዛለት የተገባው አምላክ ማንነት በተቻለው መጠን አጣርቶ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸው ሰዎችና ደቀ-መዛሙርቱ፣ ተቃዋሚዎቹም ሳይቀር እርሱን እንዲከተሉት ማንነቱን በመግለጥ በቃል በግልጽ እንደተናገራቸውና በተግባራዊ ማስረጃዎችም እንዳረጋገጠላቸው በርካታ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ያሳያሉ፡፡ ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ዮሐ 9፡1-32-38፣ "... *ዓይነ-ስውር ሆኖ የተወለደን ሰው ዓይን የከፈተ አለ ሲባል፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ማንም ሰምቶ አያውቅም። 33 ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ኖሮ ይህን ማድረግ ባልቻለ ነበር።" 34 እነርሱም፣ "ሁለንተናህ በኀጢአት ተነክሮ የተወለድህ፣ አንተ እኛን ለማስተማር እንዴት ትደፍራለህ?" ሲሉ መለሱለት፤ አባረሩትም። 35 ኢየሱስም ሰውየውን እንዳባረሩት ሰማ፤ ባገኘውም ጊዜ፣ "በሰው ልጅ ታምናለህን?" አለው። 36 ሰውየውም፣ "ጌታዬ፤ እምንበት ዘንድ እርሱ ማን ነው?" ሲል ጠየቀው። 37 ኢየሱስም፣ "አይተኸዋል፤ አሁንም ከአንተ ጋር የሚነጋገረው እርሱ ነው" አለው። 38 ሰውየውም፣ "ጌታ ሆይ፤ አምናለሁ" አለ፤ ሰገደለትም።"*

ይህ ሐዋሪው ዮሐንስ ምዕራፍ 9 ላይ በጻፈው ወንጌል ታሪኩ የሰፈረው ሰው፤ ሲወለድ ዕውር ሆኖ ተወልዶ የነበረ፣ ዕድሜው ሙሉ ሰው የሆነ (ጋብቻ ለመመስረት የደረሰ) እስኪባል የደረሰ ቢሆንም እውር ሆኖ የኖረ ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ አገኘውና አይኑን ከፍቶለት ማየት አስቻለው፡፡ ሰውየው ከመደሰቱ የተነሳ የፈወሰው ማን እንደሆነ እንኳ ሳይጠይቅ በጥድፊያ ሂዶ ስለነበር ጌታ ኢየሱስ በሌላ ቀን ሲያገኘው፣ በእኔ ታምናለህ ወይ ብሎ በጠየቀው ጊዜ ገና ያኔ ላምንህ የምችለው ያንተን ማንነት ሳውቅ ነውና ማንነትህን ንገረኝ ብሎ እንደ ጠየቀው እናያለን፡፡ ጌታ ኢየሱስም ዓይኑን ያበራለት እርሱ መሆኑን ሲነግረው ወዲው ገባውና አምኖ በመቀበል ሰገደለት፡፡

ማቴዎስ 16፡13-17፣ *"ኢየሱስ ፊልጶስ ቂሣርያ ወደተባለው አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፣ "ለመሆኑ ሰዎች፣ የሰውን ልጅ (ራሱ ጌታ ኢየሱስን) ማን ነው ይላሉ?" ብሎ ጠየቃቸው። 14 እነርሱም፣ "አንዳንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ ሌሎች ደግሞ ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ" አሉት። 15 እርሱም፣ "እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?" አላቸው። 16 ስምዖን ጴጥሮስም፣ "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" በማለት መለሰ። 17 ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ብፁዕ ነህ፤ ይህን የገለጠልህ በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም አይደለም፤" አለው፡፡* (በሌላ አባባል ጌታ ኢየሱስ አዎን እኔ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነኝ በማለት እንዲያመልኩት ራሱን እያስተዋወቀ ነበር፡፡

በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔር ማንነቱን ለሚያመልኩት እስራኤላዊያን እንደሚገባ አብራርቶ የተናገረ፣ ተጫባጭ ታምራዊ ስራዎችን ሰርቶ ያሳየ አምላክ መሆኑን ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እናያለን፡፡

ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ ለማንም ሳያዳላ ለሁሉም ፍፁም መልካምና የሚመስለው፣ የሚወዳደረው በሰማይ በምድር ማንም የሌለ፤ ብቻውን ወሰን አልባ ታላቅ የሆነ ... አምላክ መሆኑን ካላወቀ ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢ የሆነ ሕብረት ሊኖረውና

ሕብረቱም ዘላቂ እንዲሆን የሚያስችለውን ለእግዚአብሔር እንደሚገባው መገዛት/መታዘዝ ሊያሳይ አይችልም፡፡

ዘጸአት 5፡1-2፣ *"ከዚህ በኋላ ሙሴና አሮን ወደ ፈርዖን ሄደው፣ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) 'በምድረ በዳ በዓል እንዲያደርግልኝ ሕዝቤን ልቀቅ' ይላል" አሉት።*

[2] *ፈርዖንም "እንድታዘዘውና እስራኤልን እንድለቅለት ለመሆኑ ይህ እግዚአብሔር (ያህዌ) ማነው?" እግዚአብሔርን (ያህዌ) ኣላውቅም፤ እስራኤልንም አለቅም"* አለ።

ስለዚህ ፈርዖን የአግዚአብሔርን ማንነት ስላላወቀ ለመታዘዝ እምቢ በማለቱ በራሱ ሕይወትና በአገሩ ሕዝብና ንብረት፣ ሕይወትም ላይ ምን ያህል መቅሰፍት እንዳስከተለ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡

እግዚአብሔርም ራሱ ሰው ሁሉ እንዲያውቀው ስለሚፈልግ ሰው ሊያውቀው የሚያስችሉትና የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ ሰጥቷል፤ ራሱንም በተለያየ መንገድ አስተዋውቋል፣ አሁንም እያስተዋወቀ ነው፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ከሚያስተዋውቀባቸው የተለያዩ መንገዶች ጥቂት ምሳሌ ለመጠቀስ ያህል በሰማይና በምድር በፈጠራቸው በዓይን በሚታዩና በማይታዩ ፍጥረታት ድንቅ ዲዛይንና አሰራር፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ ማንነትና ከሰውም የሚፈልገው ምን እንደሆነ በዝርዝር ገልጦ በመናገሩ፣ ሰውን ለማዳን በሚሰራቸው ተዓምራዊና አስደናቂ ስራዎቹ ...ወዘተ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ በሰጣቸው የተለያዩ ማስረጃዎች አማካይነት (ተጠቅመው) ሰዎች እንዲያውቁት ምን ያህል እንደ ሚፈልግ የሚያሳዩ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ምሳሌ፡ -

***ኢሳይያስ 43፡10-13***፣ *"ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ፣ እርሱ እኔ እንደሆንሁ ትረዱ ዘንድ፣ እናንተ ምስክሮቼ፣ የመረጥሁትም ባሪያዬ ናችሁ" ይላል እግዚአብሔር። "ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም፤ ከእኔም በኋላ አይኖርም።* [11] *እኔ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም ሌላ የሚያድን የለም።* [12] *ገልጫለሁ፤ አድኛለሁ፤ ተናግሬአለሁ፤ በመካከላችሁ እኔ እንጂ ባዕድ አምላክ አልነበረም። እኔ አምላክ እንደሆንሁ፣ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ" ይላል እግዚአብሔር፤* [13] *"ከጥንት ጀምሮ እኔው ነኝ፤ ከእጄም ማውጣት የሚችል የለም፤ እኔ የምሰራውን ማን ማገድ ይችላል?" (ዮሐንስ 20፡19-30-31 ፣ ሮሜ 10፥17)*

***ዘዳ 4፡34-35*** *"አምላካችሁ እግዚአብሔር በዓይናችሁ እያያችሁ ለእናንተ በግብጽ እንዳደረገው ሁሉ በፈተና፣ በታምራዊ ምልክቶችና በድንቆች፣ በጦርነት በጸናች እጅና በተዘረጋች ክንድ ወይም በታላቅና አስፈሪ ስራዎች ከሌላ ሕዝብ መካከል አንድን ሕዝብ የራሱ ለማድረግ የቻለ አምላክ አለን? እግዚአብሔር እርሱ አምላክ መሆኑን፣ ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እንድታውቁ እነዚህን ነገሮች እንድታዩ አደረገ፡፡"*

***ሆሴ 6፥6***፣ *"ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፣ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እሻለሁና።"*

*ሆሴ 6፥3፣ “እግዚአብሔርን እንወቀው፤ የበለጠ እናውቀውም ዘንድ እንትጋ፤ እንደ ንጋት ብርሃን፣ በእርግጥ ይገለጣል፤ ምድርን እንደሚያረሰርስ የበልግ ዝናብ፣ እንደ ክረምትም ዝናብ ወደ እኛ ይመጣል።”*

ይህ ቃል እግዚአብሔርን ለማወቅ ተግተን መሰራት የምንችላቸውና የሚገቡን ነገሮች ካደረግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ እርሱን በማወቅ እያደግን እንደምሄድ የሚያሳይ ቃል ነው፡፡ አንድ ሰው ሳይንሳዊ/ምድራዊ እውቀቱን ለማሳደግ ከህጻንነት ጀምሮ ፊደል ከመቁጠር አንስቶ የዩኒቨርስቲ ምሩቅ ለመሆን ምን ያህል ዓመታት እንደ ሚያጠና ልብ ስንል መንፋሳዊ ዕውቀትም እንዲሁ እጅ አጣጥፎ በመቀመጥ እንደማይገኝ ያስገነዝበናል፡፡ ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳልና፡፡ ለስጋዊ ፍላጎቱ ማሟያ ለሚያስፈልጉ ነገሮች (ሳይንሳዊ ትምርት ማጥናት) ላይ ብቻ ከሰራ ከስጋው መበስበስና መጥፋትን ያጭዳል፤ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ረገድ በሚያስፈልጉ ነገሮች ላይ እንደሚገባው ከሰራ መንፈስ ከሆነው አምለላካችን የዘላለም ሕይወትን ያጭዳል፡፡

እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በዓይን ባይታይም ማንኛውም ሰው እንዲያውቀው የሚያስፈልጉ ራሱን የሚያስተዋውቅባቸው ነገሮች ሁሉ ስለ ሰጠ በእርሱ በኩል የተጓደለ ምንም ነገር ሳያስቀር ጨርሶ አከናውኗል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔርን ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ በማወቅ ለማደግ ማድረግ የሚጠበቅበት የራሱ ድርሻ እየተወጣ መሆን አለመሆኑን ራሱን መርምሮ በማየት ያጎደለውን ነገር ለይቶ በማወቅ የማስተካከል ግዴታ አለበት ማለት ነው፡፡

እንድናውቀውና እንድንከተለው በየትውልዱ ሁሉ ያልተቋረጠ ራሱን የማስተዋወቅ ስራ የሚሰራው እግዚአብሔር እንዳች የጎደለው ነገር ኖሮ ከእኛ ለማሟላት ፈልጎ ሳይሆን ያለ እርሱ እኛ አንዳች መልካም ነገር ሊኖረን እንደማይችል ስለሚያውቅ ነው፡፡

***ኢዮብ 35፡6-8፣*** *"ኀጢአትህስ ቢበዛ እርሱን ምን ትጐዳዋለህ? በደልህ ቢበዛ ምን ያደርገዋል?*

*7 ጻድቅ ብትሆንም ለእርሱ ምን ትሰጠዋለህ? ከእጅህስ ምን ይቀበላል? 8 ክፋትህ የሚጐዳው እንዳንተ ያለውን ሰው ብቻ ነው፤ ጽድቅህም የሚጠቅመው የሰውን ልጆች ብቻ ነው።"*

እግዚአብሔር ስለ መንፈሳዊው ዓለም በመጽሐፍ ቅዱስና በተለያዩ መንገዶች የገለጠውን ነገር ይበልጥ ባወቅን መጠን በእግዚአብሔር ላይ የሚኖረን እምነት ይበልጥ እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ማንነት በትክክል ካለ መረዳቱ የተነሳ የኃይማኖት መሪ የሆነ ሰው እንኳ ሳይቀር ለከፋ ኃጢአት ሊዳረግና ሊጠፋ እንደሚችል የአይሁድ እምነት መሪዎች ጌታ ኢየሱስን አሳች ነው ብለው እንዲገደል ማድረጋቸው ተጨባጭ ማስረጃ ነው፡፡ የሚከተለው ጥቅስ እግዚአብሔርን መፈለግ ተገቢ ከመሰለን የምናደርገው ወይም የምንተወው ሳይሆን አጥብቀን ልንዘው የተገባ መሆኑን ያሳያል፡፡

*2ዜና 15፥2 “እርሱም አሳን ሊገናኘው ወጣ፤ እንዲህም አለው፤ አሳ፣ እናንተም ይሁዳና ብንያም ሁሉ ሆይ፤ አድምጡኝ፤ እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር ስትሆኑ፣ እርሱም ከእናንተ ጋር ይሆናል፤ ብትፈልጉት ይገኝላችኋል፤ ብትተውት ግን፣ ይተዋችኋል።”*

"ብትተውት ይተዋችኋል" ሲል ስለ ተዋችሁ ራሳችሁ በነጻነት ትኖራላችሁ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከተዋችሁ እግዚአብሔር ለእናንተ ከዚህ በፊት የደርግላችሁ የነበረው በሕይወት ለመኖር የሚያስፈልጋችሁን ነገር መስጠትና ከጠላቶቻችሁም አጥር ሆኖ

መጠበቁን ወደፊትም ሊያደርግላችሁ ያቀደውን ይተዋል ማለት ነው፡፡ ይህ ሲሆን ሰው አጥሩ እንደፈረሰ ሰብል ስለሚሆን ክፉ መናፍስት የፈለጉትን ማንኛውም ዓይነት ጥቃት ሊፈጽሙበት፣ በእጁ የነበረውን ቁሳዊና መንፈሳዊ በረከትን እንዲሁም ሁለንተናዊ ጤንነት እንደፈለጉት አለከልካይ ለመንጠቅ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

የእግዚአሔር ማንነት/ባህሪያት በጥልቀት ለማወቅ ወደፊት ሰፋ አድርጎ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የሚጠይቅ ሲሆን ለአሁኑ ለመግቢያ ያህል አጠር ያለ ማብራሪያ እንመልከት፡፡

**የአግዚአብሔር ባሕሪያት፡** - የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባህርያት በ2 ይከፈላሉ፡ -

1. ተወራራሽ ያልሆኑ ባህሪያት (Incommunicable Natures of God) ሲሆኑ
2. ተወራራሽ የሆኑ ባህሪያት (Communicable Natures of God) ናቸው፤

ተወራራሽ ያልሆኑ የእግዚአብሔር ባህሪያት የሚባሉት፡ - የራሱ የእግዚአብሔር ብቻ የሆኑና ከሰውም ሆነ ከማናቸውም በሰማይና በምድር ካሉ የሚታዩና የማይተታዩ ፍጥረታት ጋር የማይጋራቸው የተለዩ የእግዚአብሔር ባህሪያት ናቸው፡፡ እነዚህም

1.1. **በህላዌው ራሱን የቻለ/ ራሱ በራሱ ሕያው ሆኖ የሚኖር**፣ ራሱን በራሱ የሚያውቅና የራሱ ባህርይ መሰረት መሆኑ ነው፣ **ራሱ በራሱ ሙሉ ብቃት ያለው፤ የማንም/የምንም ድጋፍ የማያስፈልገው ነው፡፡ (Self-Existence and Self-Sufficient)፤ መዝ 90:2; 93:2; 102:24—27**፣ ዮሐ 5፡26፣ **ዕብ 1፡12፣ 13:8; 1 ጢሞ 6:14-15; ራዕ 1:8**፣ ዘፍ 1፡1፣ col 1:17፡፡ እግዚአብሔር በማንም ያልተፈጠረ ለዘላለም በራሱ ሕያው ሆኖ የነበረ ያለና የሚኖር መሆኑ ነው፡፡

1.2. **ሁል ጊዜ በሁሉም ስፍራ በአንድ ጊዜ መገኘት የሚችል** (Omnipresence)፤ መዝ 139:7-12; ኤር 23:24፡፡

1.3. **ሁሉን የሚያውቅ** (Omniscience/ient)፤ - መዝ 139፡2-4, ኢሳ 40:28, 46:9-10, ዕብ 4:13; 1ዮሐ 3:20 እግዚአብሔር አንዳች የሚሰወርበት ነገር የሌለው በጨለማና በስውር ስፍራ የተሰራውን/የሚሆነውን በፍጥረት ልብ ያለውን ሀሳብ ሳይቀር፣ ጥንት የሆነውንና ወደፊት የሚሆነውን ነገር ሁሉ አንዳች ሳይቀር የሚያውቅ ነው።

1.4. **ሁሉን ማድረግ የሚችል**፣ የሚሳነው፣ የሚከብደው ምንም ነገር የሌለ፣ (Omnipotence፣ All powerful, All mighty) ዘፍ 17:1, 18:14 መዝ 33:6, 9; ኢሳ 40:28; ማቴ 19:26, ራዕ 19:6

1.5. **የጥበብ ፍጹም ሙላት የተሞላ** (Omni sapient, all-wise)፤ ሁል ጊዜ ስለ ማንኛውም በሚያደርገውና በሚናገረው ነገር ከሁሉ በተሻለ ጥበብ የተሞላ ነው፡፡ እርሱ ፍጹም በሆነና በማይለዋወጥ ጥበብ የተሞላ ነው፡፡

1.6. **የማይለዋወጥ፣ የማይሞት፣** የማይደክም፣ የማይተኛ፣ የማያንቀላፋ ነው፡፡ (Immutability) እግዚአብሔር በፍጹም ባህርያቱ (ማንነቱ)፣ በዓላማው(እቅዱ)፣ በህላዌው፣ በተስፋ ቃላቱ በዘመናት አይለዋወጥም፡፡
ነገር ግን ሰው ከእርሱ ጋር በሚኖረው ግንኙነት (ኅብረት) መበላሸት የተነሳ የስሜት ለውጥ ሊያደርግ (ሊጸጸት፣ ሊያዝን፣ ሊምር፣ ሊቆጣ፣ ሊደሰት፣ ሊራራ

…) ይችላል፡፡መዝ 90:2; መዝ 102፡24-27፣ ኢሳ 40፡28፣ ሚልክ 3:6; ዕብ 1፡ 10-12፣13:8፣ ያዕቆብ 1፡17

1.7. **ለዘለዓለም የሚኖር** (Eternal) የዘመኑ ቁጥር መነሻና መጨረሻ የሌለው፡፡ ዘፍ 21:33; ዘዳ 33:27; ኢሳ 40:28; መዝ 90:2).

1.8. በማንነቱ ሁሉ በተወራራሽ ባህርያቱ ጭምር **ወሰን አልባ ታላቅ** የሆነ ነው (Infinite) (ዘፍ 21:33; ዘዳ 33:27; ኢሳ 40:28; መዝ 90:2).

1.9. **ሉዓላዊ መሆኑ** (sovereign) በፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ላይ ማድረግ የፈለገውን/የመረጠውን ሁሉ ለማድረግ ሙሉ ኃይል፣ ጥበብና ሥልጣን ያለው ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የሆነው እየሆነ ያለውና ወደፊት የሚሆነው ነገር ሁሉ ላይ ሙሉ የበላይነት ስልጣን ኃይልና የመቆጣጠር ችሎታ ያለው፣ ምንም ሊቆጣጠረው የማይችል ነገር የሌለ መሆኑ፡፡
1 ጢሞ 6:15; ኢሳ 46:10).

1.10. **አለመከፋፈሉ/አይከፋፈልም** (Oneness/Simplicity) የተለያየ ክፍል ያለው ነገር በራሱ ህይወት ሊኖረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ባህርዩ ከዚህ ቀደም ይኖር ከነበረ ነገር ተሰርቷልና የማይለዋወጥ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም የሚደመረው ነገር የባህርይ ለውጥ ያስከትላልና፡፡ እግዚአብሔር በመለኮቱ አይከፋፈልም፡፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ሶስት አካላት አሉ ይህም ሲባል እግዚአብሔር የ3ቱ አካላት ስብስብ ሳይሆን "የመለኮት ሙላት" በእያንዳንዱ አካል ይኖራል ማለት ነው፡፡ ከ3ቱም አካላት ውጭ አይኖርም፡፡ ቆላ 2፡29፣

2.**ተወራራሽ** የሆኑ የእግዚአብሔር ባህሪያቱ ማለት ምንም እንኳ በጣም በተወሰነ መጠን/ደረጃ ቢሆንም በሰዎችም የሚታዩ ባህርያትን ነው፡፡ እነዚህም፡ -

ቅድስና (ቅዱስ)፣ ፍቅር፣ ፍትህ፣ ደግነት፣ መሐሪነት፣ ቸርነት፣ ርህራሄ፣ ዕውነተኛነት፣ ታማኝነትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር በሰው አእምሮ ታውቆ ሊጨረስና ሊመረመር የማይቻል ወሰን የሌለው ታላቅ አምላክ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ቀጥሎ 2ኛው ወይም 3ኛው ማን ነው የሚል ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልሱ ከእግዚአብሔር ጋር በማስተያየት 2ኛ፣ 3ኛ፣ 1, 000, 000ኛ (ሚሊዮንኛ) … ወዘተ ተብሎ ሊቀርብ የሚችል ማንም/ምንም የለም (ኢሳ 40፡25-26፣ 46፡5፣ 9)፡፡ እግዚአብሔር ብቻውን እውነተኛ አምላክ ሲሆን ሌላው ሁሉ ግን እርሱ የፈጠረው ፍጥረት ነው፡፡ ይህ አምላክ ቅዱስ ስላሴ (Trinity) በመባል ይታወቃል፡፡

ፍጥረተ-ዓለም ሁሉ የተፈጠረው ሶስቱም የስላሴ አካላት በአንድነት በመሳተፍ ሲሆን፣ ለዚሁ ተግባር ዋናው አነሳሽ ግን እግዚአብሔር አብ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡

በክርስትና እምነት ስላሴ ማለት፣ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ባህርይ አንድ የሆነና ለዘላለም በሶስት የተለያዩ ሰብዕና/አካላት (Persons) የሚኖር ማለት ነው፡፡ ሰብዕና ያለው ማለት

ዕውቀት፣ ስሜታና ፈቃድ ያለው ማለት ነው፡፡ ሶስቱ የመለኮት አካላት አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሰብዕና ያለው ነው ማለት የራሱ ዕውቀት ስሜትና ፈቃድ ያለው ነው እንጂ እንዲሁ ሰብአዊ ያልሆነ ኃይል ወይም ጉልበት አይለም ለማለት ነው፡፡ ይህ የስላሴ ትርጉም ሶስት ወሳኝ ነጥቦችን ያሳያል/ይገልጣል፡፡

1. በሰማይና በምድር ሁሉ አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ መኖሩን፡፡ ኢሳ 43፡10-13፣ 45:21-22፣ 44:6-8; ዘዳ 4:35; 6:4-5; 32:39;
2. ይህ አንድ አምላክ በሶስት ሰብዕና/አካል የሚኖር መሆኑን፡፡
3. እያንዳንዱ የስላሴ አካል ሙሉና እኩል የሆነ መለኮታዊ ባህርይና ክብር ያለው መሆኑን ነው፤

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሶስቱ አካላት እርስ በርሳቸው እኔ፣ አንተ፣ እርሱ ሲባባሉ የሚታይ ሲሆን በአንድነት ደግሞ እኛ ያሉበትም ቦታ አለ፡፡ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተቃለያየ ሰብዕና አላቸው ማለት አብ ወልድ አይደለም፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስም አብ አይደለም ማለት ነው፡፡ የስላሴ አካላት የተለያየ ሰብዕና አላቸው ማለት እኔ ከአንድ ሰው ጋር የተለያየ ሰብዕና ያለን ሆነን አንዳችን ከሌላው ለየብቻችን የተነጣጠልን እንደምንኖረው መሆናችን አይነት አይደለም፡፡ አብ ራሱን "እኔ" ወልድን "አንተ"፣ መንፈስ ቅዱስን "እርሱ" እንደሚለው ዓይነት ለማለት ነው እንጂ፡፡

ስለዚህ ማጠቃለያው በሶስት አካላት የሚኖር አንድ አምላክ አለ የሚል ነው፡፡

እያንዳንዱ የስላሴ አካል ይናገራል፣ ያመዛዝናል፣ ያስባል/ይረዳል፤ ፈቃድና ስሜት አለው፡ ፡ እነዚህ ነገሮች የሰብዕና መለያዎች/መገለጫዎች ናቸው፡፡

ደግሞም አንዱ የስላሴ አካል በሌላው የስላሴ አካል ውስጥ ይኖራል፡፡ (ዮሐ 14፡10) በስላሴ አካላት መካከል የትልቅነት (hierarchical/ontological) የበላይና የበታችነት የለም፡፡ ፍጥረታትን በመፍጠርና ሰውን በማዳን ሂደት እያንዳንዱ ባለው ሚና በመካከላቸው ተዛምዶዋዊ (relational/economical subordination) የሆነ በፈቃደኝነት አንዱ ሌላውን ማክበር/መከባበር አለ፡፡ አብ ወልድን ሰውን ለማዳን ልኳል፣ አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስን ወደ ዓለም ልከዋል፡፡ ይሄ ሚና (role/function) ምን ጊዜም በተገላቢጦሽ ሆኖ አያውቅም፡፡ ማለትም ወልድ አብን ወይም መንፈስ ቅዱስ ወልድን አልላከም፡፡ (ሉቃ 22:42; ዕብ 10:7).

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላሴ የሚል ቃል የለም፡፡ ነገር ግን የስላሴ መኖር የሚያመለክቱ/የሚያሳዩ በርካታ ጥቅሶች አሉ፡፡ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፡ -

**ከብሉይ ኪዳን፡-** ዘፍ1:1፣ ዘዳ 6:4 (ኤሎሂም- የሚል በዕብራዊያን የብዙ ቁጥር ተጠቅሟል), ዘፍ1፡26; 3:22; 11:7; መዝ 2:7፣12፣ ኢሳ 6:8 (US/ እኛ የሚል ተውላጠ ስም ተጠቅሟል)፣ 45:6-7፣ 48:16, 61:1; ምሳ 30:2-4፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን ስለ ስላሴ አስተምህሮ እንደ አዲስ ኪዳን ዘመን (አንደ አሁኑ) ግልጽ ሆኖ የሚታወቅ አልነበረም፡፡

በአዲስ ኪዳን ግን ስላሴ የሚለው ቃል አይኑር እንጂ የስላሴ አካላት በአንድ ስፍራም ሆነ በተናጠል በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተጠቅሰው ይታያል፡- ማቴ 3:16-17, 28:19; ዮሐ 1:1-4, 14,14:16-17፣ሉቃ 4:18-19፣ 2ቆሮ 3:17, 13:14፣ኤፌ 4:4-6፣ ዕብ 1:8-9, 1 ጴጥ 1:1-2፣ ራዕ 1:4-6፡፡

የስላሴ እምነት ተቃዋሚዎች የሆኑት እንደ ጀሆቫ ዊትነስ፣ ሞርሞኖች፣... ወዘተ እንደሚሉት፡-

1. የስላሴ እምነት ማለትም በሶስት ሰብዕና የሚኖር አንድ እውነተኛ አምላክ አለ ማለት፣ የስላሴ እምነት ተከታይ በ3 አማልክት የሚያምን ነው ማለት አይደለም፡፡
2. ሶስቱ አካላት የአምላክ 3 ክፍሎች አይደሉም፡፡ እያንዳንዱ የስላሴ አካል ሙሉ መለኮታዊ ባህርያት ያለው ነው እንጂ፡፡
3. እግዚአብሔር አምላክ አንድ ሰብዕና ሆኖ ሶስት ተከታታይ ሚናዎች ያሉትም አይደለም፡፡
4. አንዱ አምላክ ከሶስት ሰብዕናው ጋር የሚቃረን አይደለም፤ ምክንያቱም አንድና ሶስት የሆነበት መንገድ የተለያየ ነውና፡፡ አንድ የሆነው በባህርይ ሶስት የሆነው በሰብዕናው ነው፡፡

© ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)    2018 ዓ.ም.